# «ለአንድነትም ይሁን ለነፃነት ወሳኝ ህዝብ መሆን አለበት»

ክቡር ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ

## ክፍል አንድ

የቀድሞ የአፌድሪ ፐረዝደንት ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ በተለያዩ ሃገራዊ ገዳዮች ዘርያ ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ቀለመጠይቅ አድርገዋል:: እንደሚከተለው ቀርበዋል::

***ህዝባዊ:*** *ዶክተር ነጋሶ ሌሎች ጥያቄዎች ከማንሳታችን በፊት የት እንደተወለዱና የአስተዳደጎና የቤተሰቦችዎን ሁኔታ በተመለከተ ጥቂት ቢነግሩንስ?*

__ዶ/ር ነጋሶ:__ **የተወለድኩት ከጣሊያን ወረራ በኋላ በጳጉሜ 3 ቀን 1935 ዓ.ም በደምቢዶሎ ከተማ ነው፡ ደምቢዶሎ በድሮ ወለጋ ጠቅላይ ግዛት የቄሌም አውራጃ፣ ዛሬ ደግሞ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ወለጋ ዞን የሰዮ ወረዳ ዋና ከተማ ነች:: እናቴ ወ/ሮ ድንሴ ሾሊና አባቴ ቄስ ጊዳዳ ሶለን የዛው የደምቢዶሎ ተወላጆች ናቸው:: አባቴና እናቴ በደርግ ዘመን እኔ በጀርመን አገር በስደት ላይ እያለሁ ነው ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት፡ ሁለት ታላቅ እህቶቼና አንድ ታናሽ ወንድሜ በህይወት አሉ:: ታላቅ ወንድሜ አምባሳደር ዶ/ር ሰለሞን በ1995 ክረምት ሲያርፍ ሶስት ወንድሞቼ እኔ ሳልወለድ በህፃንነታቸው ነው የሞቱት:: ወላጆቼ በ1915 አካባቢ የካልቪኒስት ወይም የፕሬስቢታሪያን የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዮች ስለሆኑና አባቴም በጣሊያን ወረራ ጊዜ የዚሁ ሃይማኖት ተከታይ በሆነች የቤቴል ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን ቄስ ስለሆኑ ያደግሁት በዚሁ ሃይማኖት ስነ ምግባር ነው:: በኋላ ላይ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ በነበርኩኝ ጊዜ ከሜኖናይት ሃይማኖት ትምህርት የወሰድኩአቸውና አሁንም ደስ የሚሉኝ ነገሮች አሉ:: አስራ አንድ ዓመት ዕድሜ እስኪሞላኝ ድረስ ያደግሁት በደምቢዶሎ ሲሆን ከዚያ በኋላ አባቴ ለስራ ወደ ሚዛን ተፈሪ (በዛሬው የደቡብ ክልል የቤንች ማጂ ዞን) ስለተዛወሩና ለብዙ ዓመታት እዚያ ስለኖሩ ለመጀመሪያ ጊዜ በተከታታይ ለሶስት ዓመት እዚያ ከኖርኩኝ በኋላ ወደ ደምቢዶሎ ለትምህርት ብመለስም የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን እስካጠናቅቅ ድረስ በየክረምቱ ወደ ሚዛን ተፈሪ እመላለስ ነበር:: ለመጀመሪያ ጊዜ አማርኛን የለመድኩት በሚዛን ተፈሪ ነው:: አሁን አንዳንድ ቃላት በስተቀር ረስሁ እንጂ የቤንችንና የከፍቾን ቋንቋዎችንም ለምጄ ነበር:: በአስተዳደጌ አልኮል መጠጣት፣ ሲጃራ ማጨስ፣ ከጋብቻ ውጭ መባለግ፣ ዓለማዊ ዘፈን ውስጥ መሳተፍ፣ መዋሸት፣ ማታለልና መስረቅ መጥፎ ስነ ምግባር እንደሆኑ ነው የተማርኩት:: እስከ ወጣትነቴ ዘመን ይህንኑ ስነ ምግባር ጠብቄአለሁ ለማለት እችላለሁ:: በኋላ ላይ አገባሁ::**

***ህዝባዊ:*** *የትምህርት ሁኔታዎስ እንዴት ነበር? በተለይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቶን ካጠናቀቁ በኋላ ቀሪውን ትምህርቶን የት አጠናቀቁ?*

__ዶ/ር ነጋሶ:__ **አንደኛ ደረጃ ትምህርቴን የተከታተልኩት በደምቢዶሎና በሚዛት ተፈሪ ነው:: በደምቢዶሎ ቤቴል ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን ላይ ለሲደርስ በነበረው ስደት ምክንያት የመጀመሪያ ት/ቤቴ ተዘግቶ ስለነበር ለሁለት ዓመት ያህል ትምህርት ለማቋረጥ ተገድጄ ነበር:: ከዚያ በኋላ ለሁለት ዓመት ያህል በደምቢዶሎ ብርሃነ ኢየሱስ ት/ቤት ትምህርቴን መከታተል ጀመርኩ:: በመሃሉ ግን ወላጆቼ ወደ ሚዛን ተፈሪ ስለተዛወሩ አብሬ ሄድኩኝ በሚዛን ተፈሪ ግን ያን ጊዜ ከሶስተኛ ክፍል በላይ ትምህርት የሚሰጥ ት/ቤት ስላልነበረ እዚያ በኖርኩበት ሶስት ዓመት ሙሉ ጊዜዬን አጠፋሁ:: የእንግሊዝኛና የአማርኛ ቋንቋዎችን ለመማርና ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ለመዋል ግን እዚያ በነበረው የጋቸብ የአሜሪካን ሚስዮን ት/ቤት ተመዝግቤ ነበር:: በ1948 ዓ.ም ደምቢዶሎ ተመልሼ እስከ 1953 ዓ.ም ድረስ ከሶስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል በብርሃነ ኢየሱስ ት/ቤት የአንደኛ ክፍል ትምህርቴን አጠናቀቅሁ:: በነመንግስቱ ንዋይ ኩዴታ ጊዜ የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ነበርኩኝ:: ከ1954 ዓ.ም እስከ 1957 ዓ.ም በናዝሬት ባይበል አካዳሚ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ስከታተል ቆይቼ በ1958 ዓ.ም በልዑል በዕደ ማሪያም ላብራቶሪ ት/ቤት 12ኛ ክፍል አጠናቀቅሁ:: በ1955 ዓ.ም ግን በሚዛን ተፈሪ አሜሪካን ሚስዮን ት/ቤት አስተማሪ ነበርኩኝ::**

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን በበዕደ ማሪያም ት/ቤት ካጠናቀቅሁ በኋላ በኃይለ ስላሴ ዩኒቨርስቲ**

የትምህርት ፋክልቲ ገብቼ ትምህርቴን በ1963 አጠናቀቅሁ። ሜጀሬ የታሪክ ትምህርት ሲሆን ማይነሬ ላይብረሪ ሳይንስ ነበር የተከታተልኩት ትምህርት ለሁለተኛ ደረጃ መምህርነት ነበር። ትምህርቴን እንዳጠናቀቅሁ በመካነ ኢየሱስ የመዕራብ ሲኖዶስ የላሎ አይራ ት/ቤት (ምዕራብ ወለጋ) በዳይሬክተርነትና በታሪክ መምህርነት እስከ 1966 ዓ.ም አገለገልኩኝ። የየካቲት 66 አብዮት ሲፈነዳ አይራ ነው የነበርኩት። ከዚያ በመስከረም 1967 ዓ.ም በመካነ ኢየሱስ በኩል ባገኘሁት የነፃ ትምህርት ዕድል አማካኝነት በማስተርስ ደረጃ በታሪክ ትምህርቴን ለመቀጠል ወደ ጀርመን አገር ሄድኩኝ። ያኔ ዓላማዬ ቢበዛ በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ትምህርቴን አጠ ናቅቄ ወደሃገሬ ለመመለስ ነበር። የማስተርስ ድግሪዬን በእቅዴ መሠረት በ1970 ነው ያገኘሁት። ነገር ግን በዚያን ጊዜ ባገራችን በነበረው የፖለቲካ ሁኔታና በኦሮሞ ህዝብ የነፃነት ትግል ውስጥ በነበረኝ ተሳትፎ ምክንያት እዚያው ጀርመን አገር የፖለቲካ ጥገኝነት ጠይቄ እስከ 1983 ዓ.ም ቆየሁ። እስከ 1976 ድረስ በፖለቲካው እንቅስቃሴ በስፋትና በጥልቀት እየተሳተፍኩና የኑሮ ችግሮችንም እየተጋፈጥኩኝ እንደምንም ብዬ በ1976 ዓ.ም በታሪክ ትምህርት የፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪዬን አገኘሁ። የምረቃ ጽሑፌ በምዕራብ ኦሮሚያ በተለይም በሰዮ ኦሮሞ ታሪክ ላይ ነው። የማስተርስንም ሆነ የዶክትሬት ትምህርቴን የተከታተልኩት በፍራንክፈርት ጀሃን ዎልፍጋንግ ጎቴ ዩኒቨርስቲ ነው።

***<u>ህዝባዊ፡</u> አሁን ወደ ፖለቲካ ህይወትዎ እንመለስና የመጀመሪያ የፖለቲካ ተሳትፎዎ እንዴት ነበር?***

**<u>ዶ/ር ነጋሶ፡</u>** የመጀመሪያው የፖለቲካ ተሳትፎ በምንልባት ጊዜ የተለያዩ ሁኔታዎችን ለማካተት ስለሚችል የነበረውን የጭቆና አገዛዝ በመቃውም ሳደርግ በነበረው የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ ባተኩር ይሻላል። ይመስለኛል ጊዜው የ1956 ዓ.ም ክረምት ነው። ለእረፍት ወደ ደምቢዶሎ ሄጄ ነበር። ከየአካባቢው ለክረምት ዕረፍት የመጣን የሁለተኛ ደረጀ ተማሪዎች ለህብረተሰባችን በጐ ነገር ብናበረክት ይሻላል በማለት እንደየፍላጐታችን ወይ ወንጌል በማስተማር፣ ወይ በት/ቤቶችና በክሊኒኮች ህንፃዎች ግንባታ በመስራት፣ ወይም ፊደል በማስተማር እንቀሳቀስ ነበር። በነዚህ ፕሮግራሞች እንድንሳተፍ የአሜሪካን ሚሲዮን በጣም ረድቶናል። በተጓዳኝ ደግሞ ስለ አካባቢው የባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሁኔታ የሚገልጽ ድራማ ለማዘጋጀት በራሳችን ተነሳሽነት ወሰንና አንድ ድራማ አዘጋጅንና ድራማውን በከተማውና በገጠሩ ለማሳየት የአውራጃ አስተዳዳሪ የነበሩትን ደጃዝማች ገነነው በዳኔን ጠየቅን። ድራማው የፖለቲካ ይዘት ያለው መንግስትንና ሕዝብን የሚያጣላ ነው ተባልንና ድራማውን እንዳናሳይ ተከለከልን። ይህ በጣም አናደደን። ይህ ሁኔታ እያለ በዚያን ክረምት ሲካሄድ በነበረው የፖርላማ ምርጫ ያሸነፉ፣ አቶ ሲሜሶ ዴንጋ የሚባሉ መምህር ህዝብን ከመንግስት ጋር አጣላ በመባል እንዲታሠሩ ተደረጉ። በከተማው የነበሩ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችና መምህራን ስብሰባ አድርገን የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ እናድርግ ብለን ተስማማን ያገር ሽማግሌዎችንና የከተማውን ማህበረሰብ በማስተባበር ሰላማዊ ሰልፍ አደረግን። ደጃዝማች ገነነው በዳኔ ግን ስለጉዳዩ እንዲያነጋግሩአቸው የመረጥናቸውን ዘጠኝ ያገር ሽማግሌዎች አሰሩብን እነሱም ሆነ አቶ ሲሜሶ ዴንጋ እስከ ጥቅምት 1957 ዓ.ም በደንቢዶሎ ከርቸሌ ታስረው ቆይ። ከመጀመሪያዎቹ የፖለቲካ ተሳትፎዎቼ የማልረሳው የዚህ የ1956 ዓ.ም ክረምት ክስተት ነው። የገዢ መደቦችን ጠባይ ያሳየኝ ያ ክረምት ነው። እርግጥ ከዚያም በፊት ገዢ መደቦች የቤቴል ቤተክርሲቲያንና ባባቴ ላይ ሲያደርሱ የነበሩትን ስደትና እስራት አውቅ ነበር። ያ ግን በህፃንነቴ ዘመን ነበር። ይህኛው ግን ነገሮችን በግል ለመለየት ከቻልኩ በኋላ ነው። ስለዚህ ከ1956 በኋላ የነበረውን የጭቆና አገዛዝ ለመገርሰስ በሚደረገው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ለመሳተፍ ፈቃደኝነት ማሳየቴን ጀመርኩኝ። ከዚያ በ1957 ዓ.ም ይመስለኛል የናዝሬት ባይብል አካዳሚ የጋርዴን ክለብ አባላት በመምህራችን በአቶ አልማው ነጋሳ አማካኝነት ለጉብኝት ወደ አለማያ ኮሌጅ ሄድን እዚያ እያለን አበራ ዲሳሳ የሚባል የተማሪዎች ማህበር ሥአኮ አባል የነበረ ተማሪ ስለ ኦሮሞ ህዝብና ስለኢትዮጵያ ሁኔታ እንደሁም ስለኢትዮጵያና ስለዓለም አቀፍ ተማሪዎች ንቅናቄ አስረድቶን ወደ ትግል እንድንገባ ቅስቀሳ አደረገልን። ይህም ግንዛቤዬን አዳበረልኝ። ከዚያ በ1958 ወደ አዲስ አበባ መጣሁ። ወደ መጫ ቱለማ የልማትና የመረዳጃ ማህበር ስብሰባዎች መሄድ ጀመርኩኝ። አባልም ሆንኩኝ በነዚህ ስብሰባዎች ነበር ስለኦሮሞ ማንነቴና በኦሮሞ ህዝብ ላይ ተንሰራፍቶ ስለነበረው ጭቆናና ብዝበዛ እንዲሁም ስለ ትግል አስፈላጊነት የበለጠ ግንዛቤ ያገኘሁት። በተጓደኝም የኦሮሞ የሁለተኛ ደረጃና የኮሌጅ ተማሪዎች አባል

የነበሩበት የድዴሳ ዕድገት (ልማት) ማህበር አባል ሆንኩኝ:: የዚህ ማህበር አባላት የመጫ ቱለማም ማህበር አባላት ነበሩ:: የድዴሳ እድገት ማህበር ዓላማ በተለይ ሆስቴሎችን በየትላልቅ ከተሞች በማቋቋም ችግር የነበራቸውን የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች መርዳት ነበር:: የኦሮሞን ቋንቋ፣ ባህልና፣ ታሪክም ለማስተዋወቅም ዓላማ አድርጐ ነበር:: «ከነ ቤክታ» (ይህን ታውቃለህ ውይ?) የሚለው መጽሔት በዚህ ማህበር አባላት ነበር የሚታተመው:: ያም ሆነ ይህ የመጫ ቱለማና የድዴሳ ዕድገት ማህበራት በ1959 ታገዱ:: የመጫ ቱለማ መሪዎች ታሰሩ፣ አንዳንዶቹም በእስር ቤት በድብቅ አንዳንዶቹም በይፋ በተለክለሃይማኖት አደባባይ በስቅላት ተገደሉ:: እነዚህ ክስተቶችም በአመለካከቴና በእንቅስቃሴዎቼ ሂደት ላይ ተጽእኖ ነበረባቸው:: ከዚያም ከ1959 ዓ.ም ድረስ በዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ አደርግ ነበር:: በ1963 ዓ.ም ታሪኩ ደብረ ጽዮን የአአዩተማ ፕሬዚዳንት በነበረ ጊዜ የማህበሩ መማክርት አባል ነበርኩኝ:: በዩኒቨርስቲው በነበረኩኝ ጊዜ የኦሮሞውንም ሆነ የአጠቃላይ ኢትዮጵያ ህዝቦች ችግሮች እንዲፈቱ ለማድረግ በሚካሄደው ተማሪዎች እንቅስቃሴ ንቁ ተሳትፎ አደርግ ነበር:: ለኔ ለኦሮሞ ህዝብ መብቶች መታገል ለአጠቃላይ ኢትዮጵያ ህዝቦች መብቶች መከበር ከሚደረገው እንቅስቃሴ ጋር እንደማይቃረን፣ በሌላም በኩል ለአጠቃልይ ኢትዮጵያ ለዲሞክራሲያዊ መብቶች መታገል ለኦሮሞ ህዝብ መብቶች መከበር ከሚደረገው ትግል ጋር እንደማይቃረን ጽኑ አመለካከት የያዝኩት በነዚያ ዓመታት ነበር::

***<u>ህዝባዊ፡</u>*** *የተደራጀ ፖለቲካዊ ህይወት ሲጀምሩ መጀመሪያ የተደራጁት በየትኛው ፓርቲ ስር ነበር? መጀመሪያ የተደራጀ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የጀመሩት ኦነግ ጋር ነበር የሚለውስ እውነት ነው?*

**<u>ዶ/ር ነጋስ፡</u>** ኦነግ የተመሰረተው በ1966 ዓ.ም ክረምት ላይ ነበር:: ወደ ጀርመን አገር ለመሄድ ቪዛ ለማውጣት እዚህ አዲስ አበባ ነበርኩኝ:: ከዚያን ጊዜ በፊት በዩኒቨርስቲ አብረን ከነበርነው ሰዎች መሃከል አንዳንዶቹ ኦነግን በመምስረት ሲደረግ በነበረው እንቅስቃሴ ሲሯሯጡ አይ ነበር:: እኔን ግን በሂደቱ እንድካፈል አላደረጉም ነበር:: ወደ ጀርመን የሄድኩት በመስከረም መጨረሻ ላይ ስለነበር ሕዝባዊ የሽግግር መንግስት እንዲቋቋም በጠየቀው የመጀመሪያው የተማሪዎች የፀረ ወታደሪዊው ደርግ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ተካፍዬ ነው የሄድኩት:: ጀርመን አገር ስደርስ የኦሮሞ ድርጅት አልነበረም:: ስለዚህ በ1967 ዓ.ም መጀመሪያ በጀርመን አገር ከዚያም በአውሮፓ ደረጃ የኦሮሞ ተማሪዎች ማህበር መሰረትን:: ይህ የአውሮፓ ተማሪዎች ማህበር በ1970 ዓ.ም የኦነግ ህዝባዊ ድርጅት (Mass Organization) ለመሆን ስለወሰነ እስከ 1972 ድረስ በኦነግ ደጋፊነት የአውሮፓ የኦሮሞ ተማሪዎች ማህበር አባል ሆኼ ቆየሁ:: ከዚያም በ1972 ዓ.ም የኦነግ አባል ሆንኩኝ:: በማህበሩና በኔ ማሃከል በተፈጠረው ችግር ምክንያት በ1973 ዓ.ም ከኦነግ ጋር የነበረኝ ግንኙነት ተቋርጦ ስለነበረ በ1974 ዓ.ም ከኦነግ አባልነት በስርዓት (Formally) ራሴን አገለልኩኝ:: ስለሆነም የኦነግ አባልነቴ ከሁለት ዓመት ጊዜ ያነሰ ነበር::

***<u>ህዝባዊ፡</u>*** *ታድያ ከኦነግ ጋር ምን አለያየዎት? የርእዮተ ዓለም ወይ የፖለቲካ ልዩነት ነበረዎት ወይ? ልዩነት ከነበረዎት ልዩነቱን በተመለከተ ትንሽ ቢገለፁልንስ?*

**<u>ዶ/ር ነጋሶ፡</u>** ከኦነግ ጋር የተለያየሁት ከላይ እንደገለጽኩት በአውሮፓ የኦሮሞ ተማሪዎች ማህበርና በኔ መሃከል ተከስቶ በነበረው ችግር ነው:: በዝያን ጊዜ ሁለት የኦሮሞ ተማሪዎች ማህበሮች ነበሩ:: እነዚህ ሁለቱ ማህበሮች እንዲወሃዱ ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ የተለዩ ሙከራዎች ተካሄደው ውጤት ሳያገኙ ቀሩ:: የኛ ማህበር የኦሮሞ ተማሪዎች ማህበር በአውሮፓ ሲባል ሌላኛው ደግሞ የኦሮሞ ተማሪዎች ድርጅት በአውሮፓ ይባል ነበር:: የዚህኛው ማህበር አባላት አብዛኛዎቹ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር አባላትና የመኢሶን ደጋፊዎች ነበሩ:: በ1971 ዓ.ም አካባቢ ሶስት የዚህኛው ማህበር አባላት ትምህርታቸውን በሃንጋሪ ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ፍራንክፈርት መጥተው በጀርመን አገር ጥገኝነት ጠየቁ:: ከነዚህ ሶስቱ ጋር ለብዙ ጊዜ ተወያይተን ማህበሮቹ የውህደት ውይይቱን እንዲቀጥሉ ለመጠየቅ ከሁለቱ ጋር ደብዳቤ ፃፍን:: የኔ ማህበር የአመራር አባላት በደብዳቤው ላይ የኔን ስምና ፊርማ ባዩ ጊዜ በጣም ተቆጡ:: ነጋሶ ከጐበናዎች ጋር ደብዳቤ በመፃፍ የኦሮሞን ህዝብ ትግል ከዳ የሚል ፕሮፓጋንዳ አካሄድኩኝ:: ሆኖም በነሐሴ 1973 ዓ.ም በበርሊን ከተማ የተካሄደው የማህበራችን ጉባኤ የነጋሶ ጥፋት የድርጅታዊ አሰራር ጥፋት ነው እንጂ ትግሉን የመካድ ወንጀል አልፈፀመምና ለሶስት

ወር ከድርጅቱ ይገለል አለና ወሰን፡፡ እኔም ውሳኔውን ተቀብዬ ለሶስት ወራት ውጭ ቆየሁ፡፡ ውጭ ሆኜም ትግሉን መደገፌን አላቆምኩም ነበር፡፡ እንዲያውም ኦነግ፣ TPLF እና EPLF በፍራንክፈርት የመጀመሪያውን የጋር ምሽት እንዲያካሂዱ የረዳሁት እኔ ነበርኩኝ ሆኖም ከተወሰነው ሶስት ወር በኋላ እኔ አባል የነበርኩበት ቅርንጫፍ ያለ ድምጽ መብት ልትመለስ ትችላለህ ሲለኝ ይህማ የጉባኤውን ውሳኔ ይፃረራል ብዬ ከበላይ አመራር መልስ እስኪመጣ ውጭ እቆያለሁ አልኩኝ፡፡ በዚህ ሁኔታ እስከ የካቲት 1978 ዓ.ም ቆየን፡፡ የማህበራችን የጀርመን ቅርንጫፍና የፍራንክፈርት ንዑስ ቅርንጫፍ አሉታዊ ፕሮፖጋንዳ አጠናክሮ በኔ ላይ ማካሄድ ቀጠለ፡፡ ስለዚህ አባልነቴን እንደተውኩኝ በይፋ አስታወቅሁ፡፡ በመቀጠልም የአውሮፓ ቢሮአችንም ነጋሶ ከማህበሩ ተባሮአል የሚል ይፋ ደብዳቤ በተነ ኦነግም ከኔ ጋር የነበረውን ቀጥታ ግንኙነት ለረዥም ጊዜ ሲያቋርጥ እኔም አባልነቴን ሰርዣለሁ የሚል ደብዳቤ ለአመራሩ ፃፍኩኝ፡፡ የኦነግን ሰዎች እንደገና ያየሁት እዚህ አዲስ አበባ ከ1983 ዓ.ም በኋላ ነው፡፡

ኦነግ ግንባር ነው የተለያዩ የኦሮሞ ህብረተሰብ ክፍሎች አባላትና የተለያዩ አመለካከት ያላቸውን ግለሰቦች የሚወክል የኦሮሞ ብሔር ሃርነት ግምባር ነው፡፡ ከርእዮተ ዓለም አንፃር ብዙዎቹ የኦነግ አባላት ትኩረት የሚሰጡት ብሔርተኝነት ላይ ነው፡፡ እኔ ደግሞ ለኦሮሞ ብሔር ሃርነት ብንታገልም ጉዳዮችን ከመደብ አንፀር ማየት አለብን የሚል አመለካከት ነበረኝ፡፡ ስለሆነም የትግል አጋርነታችን ከሌሎች የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች ጋር መሆን አለበት የሚል አቋም ነበረኝ፡፡ ይህም በመሆኑ በአሰራር ላይ ልዩነቶች ገጥመዋል፡፡ በሌላም በኩል የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄን በተመለከተና ስለ አፈታቱም ልዩነቶች ነበሩት፡፡ እኔም እንደ ኦነግ የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄ የኮሎኒያል ጥያቄ ነው የሚል አቋም ነበረኝ፣ አሁንም እንደዚያው ነው አቋሜ፡፡ ኦሮሚያ የተወረረችው በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም ነው በዚህ በዘመነ በኢምፔሪያሊዝም የተካሄደ ወረራ ከኮሎኒያሊዝም ውጭ ሊሆን አይችልም፡፡

ከዚህ አንፃር ከኢህአፓ፣ ከመኢሶን ከኢሰፓና ከኢህአዴግም የተለየ አቋም አለኝ፡፡ እነዚህ ድርጅቶች የኦሮሞን ጥያቄ ኮሎኒያል ጥያቄነት አይቀበሉም፡፡ ስለሆነም ከነሱ ጋር አሁንም ልዩነት አለኝ፡፡ ከኦነግ ጋር ያለኝ ልዩነት ከዚህ አንፃር ሳይሆን በኦሮሞ ህዝብ ላይ የተጫነው ቅኝ ግዛት ምን ዓይነት ቅኝ ግዛት ነው በሚለው ላይ ነው፡፡ በኔ አቋም መሰረት በኦሮሚያ ላይ የተጫነው ኮሎኒያሊዝም በፓለስቲና፣ በዝምባብዌና በደቡብ አፍሪካ የታየው ዓይነት የሰፋሪ ኮሎኒያሊዝም ነው፡፡ በዚህ ዓይነት የቅኝ ግዛት ስርዓት ወራሪው ድንበር ተሻግሮ የመጣና አንድን ህዝብ ይይዛል፡፡ የፖለቲካ ስርዓቱን ይዘረጋና ይቆጣጠራል ኢኮኖሚውን ለገዢው መደብና ለደጋፊዎቻቸው ጥቅም እንዲውል ያደርጋል የተያዘውን ህዝብ ባህል ቋንቋና ሃይማኖት ይጨቁናል በዚህም የተያዘው ህዝብ ማንነት እንዲጠፋ ለማድረግ ይጥራል የሰፋሪ ቅኝ ግዛት የገዢ መደቦች ስርዓቱን ለማስፋፋትና ለማቆየት ራሳቸውን ስለማይችሉ ባንድ በኩል ከተወረረው ህዝብ መሃከል የተወሰነውን ክፍል እየመለመሉ በአገልጋይነት ይጠቀሙባቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከውጭ ኃያላን መንግስታት ጋር ይሻረኩና የመሳሪያ፣ የገንዘብና የእውቀት ድጋፍ ያገኛሉ፡፡ ለዚህም ውለታቸውን ለኃያላኑ አገሮች በተለያየ መንገድ ይከፍላሉ፡፡ ስለሆነም በዚህ ዓይነት ቅኝ ግዛት የተያዘ ህዝብ ትግል የሚያነጣጥረው ከቅኝ ገዢዎቹ ጋር በሚያከሩት የህዝቡ ተወላጆች በቅኝ ግዛቱ የገዢ መደብና ደጋፊዎቻቸው ቅኝ ገዢዎቹን በሚረዱ የውጭ ሃይሎች ላይ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ የሃርነት ትግል ዓላማና ግብ የሰፋሪ ቅኝ ግዛት የገዢ መደቦች ስልጣናቸውን ለተመረረው ሰፊ ህዝብ እንዲለቁ ማድረግ ነው፡፡ ሰፋሪ ቅኝ ገዢዎች መቼም ቢሆን አናሳዎች ስለሆኑ እነዚህ አናሳዎች የፖለቲካ ስልጣኑን ለተያዘው ሰፊ ህዝብ በመልቀቅ እዚያ በሰፈሩበት ወይም በሚኖሩበት አካባቢ የዲሞክራሲያዊና የሰብአዊ፣ የቋንቋና የባህል፣ እንዲሁም የሃይማኖትና የኢኮኖሚ መብታቸው እየተጠበቀላቸው በአብላጫው የነባር ህዝብ መንግስት ስር ለመተዳደር ይገደዳሉ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል በዝምባብዌና በደቡብ አፍሪካ የሆነው ይህው ነው፡፡ በኦሮሚያና በነሱ ቅኝ ገዢዎች መሃከል ያለው ልዩነት የሰፋሪ ቅኝ ገዢዎቹ የዘር ወይም የቀለም ልዩነት መሆኑ ብቻ ነው ሰፋሪ ቅኝ ገዢዎች በቅኝ ግዛታቸው ለረጅም ጊዜ ለብዙ ትውልድ ሲኖሩ ስለነበር በነበሩበት አካባቢ መብታቸው ተጠ ብቆላቸው ይኖራሉ እንጂ ከዚያ ለመልቀቅ አይገደዱም፡፡ በዚህ ዓይነት የጥያቄው አፈታት ላይ ከኦነግ ጋር የአቋም ልዩነት ነበረኝ፡፡ ኦነግ ሲከተል የነበረው አቅጣጫ የፀረ ኮሎኒያሊዝም ትግል በማካሄዱ ነፃ የሆነች የኦሮሚያን ሪፐብሊክ ማቋቋም ነው፡፡ ሌላው ከኦነግ ጋር የነበረኝ ልዩነት ነፃነትን ወይም አንድነትን በተመለከተ ማን ይወስን በሚለው ላይ ነጥብ ላይ ነው፡፡ በኔ በኩል ለአንድነትም ሆነ ለነፃነት ወሳኙ ህዝቡ መሆን አለበት የሚል ጽኑ አቋም አለኝ፡፡ እነዚህ አማራጮችን በተመለከተ ኦነግ ነፃነት ሲል የኔ አቋም ደግሞ ዲሞክራሲያዊ አንድነት ነው፡፡

ስለዚህም ነው በሕገ መንግስታችን የተቀመጠውን የፌዴራል ስርዓት የደገፍኩትና የምደግፈው።

***<u>ህዝባዊ፡</u>* አውሮፓ ውስጥ ጀርመን አገር በሚኖሩበት ጊዜ በየትኛው የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ይሳተፉ ነበር? እንደሚባለው ብቻዎን የፖማቲካ ፕሮግራም ነድፈው መንቀሳቀስ ጀምረው ነበር ይባላል። ይህ እውነት ከሆነ ይህን ያደረጉበት ምክንያት ምን ነበር? ከኢህአዴግ ጋርስ መቼና እንዴት ተገናኙ?**

**<u>ዶ/ነጋሶ፡</u>** ከላይ እንዳብራራሁት የተሳተፍኩበት የፖለቲካ የመጀመሪያው ድርጅት ኦነግ ነው። የኦነግ አባል የሆንኩት በጀርመን አገር በነበርኩኝ ጊዜ ያውም በጣም አጭር ለሆነ ጊዜ ነው። ኦነግን ከለቀቅሁ በኋላ እስከ 1981 ዓ.ም አካባቢ የየትኛውም የፖለቲካ ድርጅት አባል አልነበርኩም። ከ1974 እስከ 1975 ዓ.ም ለአንድ ዓመት ተኩል ያህል ከሌሎች ከኦሮሞ ተማሪዎች ማህበር ከለቀቁ ግለሰቦች ጋር አንድ «ጉጨ ደርገጐ» የሚባል የኦሮሞ ወጣቶች ድርጅት ለማቋቋም ጥረት አድርገን አልተሳካልንም። አንድ መጽሔትም ማሰራጨት ጀምረን ነበር ሆኖም አልተሳካልንም በ1975 ዓ.ም ሁለት ግለሰቦች ብቻ ቀረን። ስለዚህም ድርጅቱን አፈረስን በ1977 ዓ.ም የኦሮሞ ተማሪዎች ማህበር ውስጥ ችግር ተፈጠረና ብዙዎች ማህበሩን ለቀው በፊት የኦሮሞ ተማሪዎች ድርጅት አባላት ከነበሩ ግለሰቦች ጋር ሆነው በአውሮፓ የኦሮሞዎች ማህበር (TOA) መሰረቱ። በ1978 ዓ.ም ይህን ድርጅት በአባልነት ተቀላቀልኩኝና እስከ 1983 ድረስ ማህበሩን ሳገለግል ቆየሁና ትቼ ወደ ኢትዮጵያ መጣሁ። እነዚህ ሁለቱ ድርጅቶች ሕዝባዊ (Mass) ድርጅቶች ነበሩ እንጂ የፖለቲካ ድርጅቶች አልነበሩም። ከየትኛውም የፖለቱካ ድርጅቶች ጋር ግንኙነትም ትብብርም አልነበራቸውም። በሌላ በኩል አንዳንድ በአውሮፓ የኦሮሞዎች ማህበር (TOA) ውስጥ የነበርንና በፊት ከመኢሶን፣ ከኢህአፓና ከኦነግ በለቀቁና በአውሮፓ በካናዳና በዩኤስኤ ሲኖሩ በነበሩ ግለሰቦች ጋር ተገናኝተን አንድ የፖለቲካ ድርጅት ማቋቋም አለብን በሚል አቋም ላይ ደርሰን አሁን በሁለት ተከፍሎአል የሚለውና የኦሮሞ ህዝብ የሃርነት ድርጅት (OPLO) የሚባለውን የፖለቲካ ድርጅት በ1981 ዓ.ም አካባቢ አቋቋምን። በነዚህ ሁሉ እንቅስቃሴዎች ከሌሎች ጋር በጋራ ነው እንጂ ብቻዬን ፕሮግራም ነድፌ ብቻዬን የተንቀሳቀስኩበት ሁኔታ አልነበረም። በአውሮፓ የኦሮሞዎች ማህበርም ሆነ የኦሮሞ ህዝብ ሃርነት ድርጅት ከኦነግ በተለየ አመለካከት ምክንያት ከሌሎች የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች ጋር የትግል አጋርነት መፍጠር አለብን የሚል አቋም ስለነበራቸው ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ ከኢህአዴግ ጋር ግንኙነት ፈጥረው ነበር። ከ1969 ዓ.ም ጀምሮ ከህወሓት ጋር ግንኙነት ነበረኝ። በፍራንክፈርት ከነበሩ ወኪሎቹ ጋር ስንደጋገፍ ነበርን። ከሻዕቢያ ጋርም እንዲሁ ስለዚህ TOA እና OPLO ከኢህአዴግ ጋር ግንኙነት ሲፈጥሩ ለኔ ደስታዬ ስለነበር ግንኙነቱ እንዲጠናከር የቻልኩትን ያህል ተንቀሳቅሼ ነበር። ሆኖም ነገሮች እንደተመኘሁት አልሆኑም። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለን የኦህዴድን መፈጠር ሰማን ኦህዴድና TOA ጥሩ ግንኙነት በመፍጠር ላይ እያሉ የ «ዱላ ከልሰማ ወልቅጡማ» ዜና ደረሰን። ይህ ክስተት እኔ በነበርኩባቸው ድርጅቶች ውስጥ ክፍፍልን አስከተለ። አብዛኛዎቹ አባላት ይህ ዘመቻ የዳግም ቅኝ ግዛት እንቅስቃሴ ነው። በወቅቱ የኢህአዴግን እንቅስቃሴ መደገፍ ማለት የትግሬ ቅኝ ግዛት እንቅስቃሴ ነው የሚል አቋም ወሰዱ። ጥቂቶቻችን ግን ዘመቻው ኦሮሚያን ማዕከሉ ያደረገውን የሰፋሪ ኮሎኒያልዝምና የደርግ ስርዓትን ለመገርሰስ የሚረዳ ሊደገፍ የሚገባ ነው የሚለውን አቋም ያዝን በዚሁ አቋም ላይ በመመስረት ነበር በግንቦት 1983 ዓ.ም ወደ አገር የመጣሁትና ሁኔታውን አጥንቼ ወደ አውሮፓ የተመለስኩት። አውሮፓ እስከ ሐምሌ መጨረሻ ቆየሁና ከድርጅቶቹ በፅሑፍና በይፋ ተሰናብቼ ወደ ኢትዮጵያ ተመለስኩ የኦህዴድ አባል እስከሆንኩበት ጊዜ ድረስ የፖለቲካ ድርጅት አባልነት ታሪኬ ይኸው ነው። ለአጫጭር ጊዜያት የኦነግና የኦህነግ (OPLO) አባል ነበርኩኝ። የራሴን ድርጅት አቋቁሜ አላውቅም። በዚህ ዓይነት ትግልም፣ ማለትም ግለሰብን ማዕከል ያደረገ ድርጅት አልደግፍም ነበር። ስለሆነም የራሱን ፕሮግራም ነድፎ የፖለቲካ ድርጅት አቋቁሞ ተንቀሳቅሶ ነበር የሚለው የሐሰት ወሬ ነው። የዚህን ዓይነት ወሬ የሚያናፍሱት ጤነኞች አይመስለኝም።

***<u>ህዝባዊ፡</u>* ኢህአዴግ ውስጥ ከኦሆዴድ ጋር ነበር ተደራጅተው መታገል የጀመሩት፣ ኦህዴድ የርስዎን ፖለቲካዊ አመለካከትና ፍላጎት በትክክል አስተናግዷል ብለው ያምናሉ? እንደሚታወቀው ኦህዴድ በአብዛኛው ወታደሮች በነበሩ የተገነባ ድርጅት ሲሆን እርስዎ ደግሞ ሙሁር ነበሩ። ከዚህ ማሕበራዊ ቦታችሁ የተነሳ የሚንፀባረቅ ልዩነት ነበርን?**

**ዶ/ር ነጋሶ:** ኦህዴድ ሲመሰረት በስብሰባው ላይ ለመገኘት ከፍተኛ ፍላጐት ቢኖረኝም በተለያዩ ችግሮች ምክንያት አልተሳካልኝም:: የኦሮሚያን ጋዜጣና የድርጅቱ ፕሮግራም እዚያው ጀርመን አገር ነው የደረሰኝ:: የ1982 ዓ.ም ፕሮግራሙ የኔን ፖለቲካ አመለካከትና ፍላጐት በትክክል አስተናግዶልኛል:: ፍላጐቴ የደርግ አገዛዝና የሰፋሪ ኮሎኒያሊስቶች ስርዓት (በሌላ አነጋገር የነፍጠኛ ስርዓት) እንዲገረሰስ፣ የኦሮሞ ህዝብ በኦሮሚያ ራሱን እንዲያስተዳድር፣ የኦሮሞ ህዝብ ያለውን የተፈጥሮና የሰው ኃይል ሀብት ተጠቅሞ ክልሉን በማልማት ከኢኮኖሚና ማህበራዊ ችግሮች እንዲላቀቅ፣ በቋንቋው እንዲጠቀም፣ ባህሉንና ታሪኩን እንዲንከባከብ፣ የኦሮሞ ህዝብ የዲሞክራሲያዊና የሰብአዊ መብቶች እንዲከበሩና፣ የኢምፔሪያሊዝም ብዝበዛና ተጽእኖ እንዲያበቃ ነበር:: በ1982 ዓ.ም የኦህዴድ ፕሮግራም እነዚህን ሁለ ዓላማዎችና ግቦች ይዛ ነበር:: ስለሆነም ኦህዴድን በነሐሴ 1983 ተቀላቀልኩኝ:: እነዚህ ዓላማዎችና ግቦችም ተግባራዊ እንዲሆኑ በንቃት ስንቀሳቀስ ነበርኩኝ ብዬ አምናለሁ::

እንደ እውነቱ ከሆነ ለኦህዴድ አባላት ማህበራዊ ቦታዎች ልዩነት ቦታ ሰጥቼ አላውቅም:: እኔ ምሁር ነኝ እነሱ ወታደሮች ነበሩ የሚል ስሜት ተፈጥሮብኝ አያውቅም:: የአባላትን ማህበራዊ ቦታ ለማጥናትም ፍላጐት አልነበረብኝም የኔ ፍላጐት አባላት ፕሮግራሙን ተቀብለው ለተግባራዊነቱ በንቃት ይታገላሉ ወይ የሚለውን ማየት ነበር::

ፕሮግራሙን ተቀብለው በድርጅቱ ሕገ ደንብና መምሪያ መሰረት ከመንቀሳቀስ ከተንቀሳቀሱ አባላት ምሁር ይሁኑ፣ ወታደር፣ ወይ ነጋዴ ወይ አርሶ አደር ለኔ ሁሉም ንጾዎች ነበሩ:: በአሰራር ላይ ችግሮች ሲፈጠሩም ችግሮቹን በዚህ ዓይነት የማህበራዊ ቦታ ላይ ስለተመሰረቱ ነው:: የሚል አመለካከት አልነበረኝም:: ይልቁንም እኛ ሁላችን የንዑስ ከበርቴ ማህበራዊ ቦታ እገነዘብ ነበር:: ስለሆነም ኦህዴድ የአዲስ ገዢ መደብ ድርጅት ይሆናል የሚል ፍራቻ ነበረኝ:: በ1989 ዓ.ም ባካሄድነው ግምገማም ይህ ሁኔታ መፈጠር ላይ እንደነበረ ስላየን ነበር የማስተካከል እርምጃ የወሰድነው ከ1993 ዓ.ም ወዲህ ያ የፈራነው ሁኔታ እንደገና ተፈጥሮ በመጠናከር ላይ ነው የሚል ፍራቻ አለኝ::

***ህዝባዊ:*** *ዶክተር ነጋሶ በሽግግሩ ጊዜ በኮንፈረንሱ ከተሳተፉትና ቻርተሩን ካፀደቁት የፖለቲካ ሰዎች አንዱ ነበሩ:: ቻርተሩን አሁን ተመልሰው ሲያዩት ጥንካሬዎቹንና ጉድለቶቹን ሊያስታውሱ ይችላሉን?*

**ዶ/ር ነጋሶ:** አይ፣ በሽግግሩ ጊዜ በኮንፈራንሱ ላይ አልተሳተፍኩም በግንቦት 21 ቀን 1983 ዓ.ም ወደሃገር ገባሁና በሰኔ መጨረሻ ወደ ጀርመን አገር ተመልሼ በሐምሌ ወር መጨረሻ ተመልሼ ወደሃገር መጣሁ:: ቻርተሩን በማጽደቅ ሂደት ላይ ለመሳተፍ ዕድል አላገኘሁም:: ቻርተሩ የፀደቀው በሐምሌ ወር የመጀመሪያዎቹ ሳምንታት ነበር:: የቻርተሩን ጥንካሬዎች በተመለከተ ከፀደቀ በኋላ እንዳነበብኩት የኢትዮጵያን መሰረታዊ ችግሮችን ለይቶ መፍትሄው የዜጐች የተናጠልና የኢትዮጵያ ህዝቦች ችግሮች የሚፈቱት የዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸው ሲከበሩ ነው በማለት ለዚህም ሁኔታን ለማመቻቸት ቃል የተገባበት ሰነድ ነው:: ድክመቱ ግን ሁለት ቅድመ ሁኔታዎችን ማስቀመጡ ነበር:: አንደኛው ቅድመ ሁኔታ በሽግግር መንግስቱ የሚሳተፉት የተለያዩ መስፈርቶችን የሚያሟሉ መሆን አለባቸው በማለት የመደራጀትና በነፃ የመንቀሳቀስ መብቶችን በመገደብ አንዳንድ ነባርና በህብረተሰቡ ውስጥ መሰረት የነበራቸውን ድርጅቶች ማግለሉ ነው:: በዚህም እነ ኢሠፓ ኢህአፓና እነመኢሶን እንዲገለሉ ተደርጓል:: ይህ የቻርተሩ ድክመት ችግር እንደፈጠር አይተናል:: ከወንጀል ነፃ የሆኑ የኢሠፓ አባሎችም እንዲደራጅ የሚፈቅድ ሁኔታ አልተመቻቸም:: በሶሻሊዝምና በኮሚኒዝም ርእዮተ ዓለም ዙሪያ ዜጐች የመደራጀት መብት እንዳላቸው አልተፈለገም ነበር:: ሌላው ድክመት የብሔር ብሔርሰቦች ጥያቄን የመመለስ አካሄድ ነው:: በቻርተሩ የተቀመጠው ቅድመ ሁኔታ ዲሞክራሲያዊነት ኢትዮጵያን እንመሰርታለን የሚል ነበር:: በመሆኑም ለብሔር ብሔረሰቦች ሃርነት ይታገሉ የነበሩት ወይ ከመጀመሪያው ወይም ደግሞ ከሂደቱ እንዲገለሉ ተደርገዋል:: መሆን የነበረበት የጋራ ሽግግር መንግስት ተቋቁሞ ድርጅቶች የፈለጉትን ፕሮግራም ይዘው ከተንቀሳቀሱ በኋላ ህዝባዊ መንግስት በምርጫ እንደተቋቋመ በነፃነት ወይም በአንድነት ላይ ህዝበ ውሳኔ እንዲካሄድ ሁኔታን ለማመቻቸት መንገድ የሚከፍት መሆን ነበረበት:: ይህ

ባለመሆኑ ችግሮች እንደተፈጠሩና ችግሮችም እየተባባሱ መሄዳቸውን አሁን እያየን ነው፡፡ የኤርትራንም ጥያቄ በመፍታቱ በኩል በሽግግር ጊዜ የህዝብ ውሳኔ እንዲካሄዱ መንገድ መክፈቱ ድክመት ነበር፡፡

***<u>ህዝባዊ፡</u>*** *በሽግግሩ ወቅት እንደገና ከኦነግ ጋር ተገናኝተዋል፡፡ ይህ ሁኔታ ለርስዎ የፈጠረው ችግር ነበር ወይ? የኦነግ አባላትስ እርስዎን እንዴት ይመለከትዎት ነበሩ?*

**<u>ዶ/ር ነጋሶ፡</u>** ወደ ኢትዮጵያ ከግንቦት እስከ ሰኔ ወደ ሃገር በመጣሁ ጊዜ በደምቢዶሎ፣ በነቀምቴና በአዲስ አበባ አንዳንድ የኦነግ አመራር ድርጅቶችን አግኝቼ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ የገለጽኩላቸው በለውጡ ሂደት ለመሳተፍ ዝግጁ መሆናቸው ትክክል እንደነበርና ኦህዴድን ጨምሮ ከሌሎች የኦሮሞ ድርጅቶች ጋር ተባብረው በመስራት የኦሮሞን ህዝብ መብቶች እንዲያስከብሩ ነበር፡፡ ከኦነግ ጋር ለብዙ ዘመናት ተለያይተን ስለነበርና በዚያን ጊዜም በሱዳን በኩል ወደ አገር የገባሁትና እስከ ደምቢዶሎም ለመሄድ የቻልኩት በኦህዴድ/ኢህአዴግ ድጋፍና የሰራዊቱ አባላት አጃቢነት ስለነበር የኦነግ ሰዎች በጥርጣሬ ነበር ሲያዩኝ የነበሩት ወደ ኦነግ ለመመለስ እኔም አልጠየቅሁም እነሱም የዚህ ፍላጐት ፍንጭ አላሳዩኝም ኦህዴድን እንደ ጉበናዎች ድርጅት ያዩ ነበር፡፡ ኦህዴድ ከኢህአዴግ እንዲለይ ይፈለጉ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ልንስማማ አልቻልንም ነበር፡፡ በሐምሌ ወር መጨረሻ እንደገና ወደ ኢትዮጵያ ከተመለስኩ በኋላ የኦነግን ሰዎች ሳገኝ የነበረው የሽግግር መንግስት ከተቋቋመ በኋላ በተወካዮች ም/ቤትና በሚኒስትሮች ም/ቤት ስብሰባዎች ላይ ነበር፡፡ በተጨማሪም በመርጫ ኮሚሺንም አብረን ሰርተናል፡፡ ኦነግ ከሽግግሩ ሂደት እስከወጣበት ጊዜ ድረስ በነዚህ መድረኮች አብረን ከመስራትና ባንደንድ ጉዳዮች የጋራ አቋም በመውሰድ ባንዳንድ ጉዳዮች ደግሞ የተለያዩ አቋሞች ከመውሰድ በስተቀር የተለየ የቅርብ ግንኙነት አልነበረንም ይልቁንም ኦነግ ሰፊ የፕሮፓጋንዳ ጦርነት እያካሄድኩኝ ነበር፡፡ ኦሮሞም አይደለም እስከ ማለት ደርሶ ነበር፡፡ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬድዮ ሲተላለፍ በነበሩት ፕሮግራሞቹም ስድብ ያወርድብኝ ነበር፡፡ ስሜንም በመቀየር «ነጋሲ ግደይ» ይለኝ ነበር፡፡ በኔ ላይ እንኳ የስድብና የፕሮፖጋንዳ ያካሄደብኝም ነበር እንጂ ሌላ ምንም አላደረገኝም ነገር ግን በዘመዶቼ ላይ ብዙ ችግሮች አድርሶአል፡፡ ታላቅ እህቴንና ባልዋን እንዲሁም ታናሽ ወንድሜን በኔ ምክንያት አስሮ ነበር፡፡